# ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት



ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ ።

www.ethiopianorthodox.org

በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ቃል ተሰማ ፤ ማቴ፡ ም፡ ፫ ቁ፡ ፲፫—፲፯ ።

ይህ የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን መነሻ ነው ። የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በኦሪት ብዙ ጊዜ ቢነገርም እንደ አሁኑ ግልጥ ሆኖ አይታይም ነበር ። ነገር ግን የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ግልጥ ሆኖ የሚታየው በሐዲስ ኪዳን ነው ። መነሻውም ይህ ነው ፤ ወልድ በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል ፤ አብ ከሰማይ ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሏል ። መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል ።

ቅዱስ ቄርሎስ በሮማ አቈጣጠር «ከ፯ኛው ሰዓት አስቀድሞ በግዕዝ ጥር ፲፩ ቀን በ፲ ሰዓተ ሌሊት ሁለቱ ማለት ጌታና ዮሐንስ ወደ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ሔዱ ። ውኆዎችም እንደሞቀ ውኃ ፈሉ ። ከተጠመቀም በኋላ ሰማይ ተከፈተ ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በላዩ ላይ ተቀመጠ ። ከሰማይም እንደመብረቅና ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ቃል ተሰማ ። ቃሉም እንዲህ የሚል ነው ። የምወደው ልጄ ይህ ነው ይህ ክርስቶስ ነው ፤ በ፴ ዘመን ከዮሐንስ የተጠመቀው ብሎ ሉቃስ እንደተናገረ» ይላል ።

ጌታችን ወንጌለ መንግሥቱን አስተምሮ ለሰው ልጅ ሲል ራሱን ሠውቶ በሥልጣኑም ራሱን ከሙታን ከስነሣ በኋላ ወደ አባቱ በሚያርግበት ጊዜ ያንድነትንና የሦስትነትን ትምህርት (ምሥጢረ ሥላሴን) ከሁሉ በበለጠ መንገድ ገልጦ አስተምሯል ። ቃሉም ይህ ነው «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ



ቅዱስም ስም አጥምቋቸው» ከተጠመቀ በኋላም ዮሐንስ ለማስተማር ከበረሃ ወደ ከተማ መጥቷል ። ጌታ ለመጾም ፤ ለመጸለይ ወደ በረሃ ሄዷል ። ዮሐንስ ወደ ግዞት ቤት በገባ ጊዜ ጌታ ለማስተማር ወደ ከተማ መጣ ። ወንጌለ መንግሥቱንም ማስተማር ጀመረ ፤ ትምህርቱም እንደመጀመሪያው የዮሐንስ ትምህርት «ንስሓ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና» የሚል ነበር ።

## ምዕራፍ ፪ ።

## የንስሓ ጥምቀት ።

የኦሪቱ ጥምቀት የንስሓ ጥምቀት ነበር ፡ አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቶ ሲናዘዝ በውኃ ይጠመቅ ነበር ፡ ውኃ የማንጻት ምልክት ነው ። በኦሪት የኦሪትን ትእዛዝ የተላለፈ ሁሉ እንደርኵስ ይቈጠር ስለነበር ፡ ከርኵሰቱ የሚነጻው በውኃ በመታጠብ ነበር ። ዘሌ፡ . . ፲፭፡ ፰ በአገራችንም ያሉ ፈላሾች አንድ ነገር በነኩ ጊዜ ፡ ሩጠው ከባሕር ይገባሉ ። የአይሁድም ክህናት ፡ አንድ ከአይሁድ እምነት ከኦሪት ውጪ የሆነ ሰው ወደ ኦሪት እምነት ሲገባ፡ በውኃ አጥምቀው ነበር የሚቀበሉት ፤ ማቴ፡ ም፡ ፳፫ ቁ፡ ፲፭

በዚህ ዓይነት ልማድ ዮሐንስ ያጠምቀው የነበረው ጥምቀት የንስሓ ጥምቀት ነበር፤የጌታም ደቀ መዛሙርት እንዲሁ የንስሓ ጥምቀት ያጠምቁ ነበር ፤ ነገር ግን ይህ ጥምቀት ልጅነትን አያሰጥም ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፫ ።

### የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አሪቱ ልማድና ሥርዓት ኃጢአት ኑሮበት ኃጢአቱን ለማስተሥረይ የንስሐ ጥምቀት ለመጠመቅ ወይም እንደሐዲስ ኪዳን ትምህርት ሁለተኛ ተወልዶ ፥ የጸጋ ልጅነት ለመቀበል አይደለም ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ፥ የጠፋውን የሰውን ልጅ ለማዳን ነው ። ለእኛ ምሳሌ ለመሆን ፥ ብዙ ዓይነት ሥራዎች ፥ እየሠራ አሳይቶናል ። ሁሉም ለእኛ መዳን መሣሪያዎች ናቸው ። ዮሐንስ አፈ ወርቅ «ከኃጢአት በስተቀር ፍጹም ሰው ሆነ ፤ እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደ ባሪያ ታየ ፤ ወንጌሉን ያስተማሩ ሐዋርያት እንደ መሰከሩ» ይላል ።

አባ ሕርያቆስም ‹ከኃጢአት በስተቀር ሕግን ሁሉ ፈጸመ ፤ በዮርዳኖስ በዮሐንስ ዕጅ ተጠመቀ ፤ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ መከራ ተቀበለ» ይላል (ቅዳሴ ማርያም) ።

ቅዱስ ኤፍሬምም ይህን ሐሳብ በመደገፍ «እግዚብሔር ከኃጢአት በስተቀር እንደ እኛ ፍጹም ሰው ሆነ» ይላል (ውዳሴ ማርያም) ።

ጌታችንም ሲያስተምር አንድ ጊዜ የነበረው ልማድና ሥርዓት እንዲጠፋ ፥ አላደረገም ። ግን ቀስ በቀስ በትምህርት እንዲለወጥ ለማድረግ ነበረ ዓላማው ። ፋሲካ ፤



በዓለ ሠዊት ፤ በዓለ መጸለት ፤ የመሳሰሉትም የአይሁድ ታላላቅ በዓላት ቀስ በቀስ በጥምቀቱ ፤ በሞቱ ፤ በትንሣኤው ፤ በጰራቅሊጦስ እስኪለወጡ (እስኪተኩ ድረስ፥በኢየሩሳሌም እየተገኘ ፥ ያከብራቸው ነበር ።

መሥዋዕቱም በራሱ መሥዋዕትነት እስኪተካ ድረስ፥ እንዲለወጥ፥ አላስገደደም። ማንም ቢሆን የነበረውን ፤ ከአባቱ ሲያያዝ የመጣውን ባህልና ልማድ ፥ ትምህርትና ሥነ ሥርዓት ለመለዋወጥም ፤ ለማሻሻልም ቢሞክር ቀስ በቀስ በነዋሪውና በተተኪው ነገር መካከል ማስረዳት አሮጌው የሚተካው ፤ አዲሱ ነገር ተመሳሳይ እንጂ ፈጽሞ የተለወጠ መሆን ስለሌለበት ጌታም አሪትን ለመፈጸም እንጂ ለመሻር ስለ አልመጣ ሊሻሻሉ የተፈለጉትን ነገሮች በትምህርትና በሥራ ለወጣቸው ፤ ይህም ሚዳዊውን ሥርዓት ነው ኤፌሶን ፬ ፲፫ ።

ከላይ እንደ ተናገርነው ዮሐንስ ያጠምቅ የነበረው የንስሓ ጥምቀት ነበር ። በኋላም ክርስቶስ ማስተማር ሲጀምር ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ የንስሓ ጥምቀት ያጠምቁ ነበር ። ጌታ ግን የንስሐን ጥምቀት ሳይሆን የልጅነትን ጥምቀት አስተማረ ። ኒቆዲሞስን «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ሁለተኛ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ። ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው» በማለት ‹ልጅነት ጥምቀትን አስተማረው ። ዮሐ ም ፫ ቍ ፭—፮ ።

www.ethiopianorthodox.org

ትን የሚያገኝበት ፤ ኃጢአትን የሚያስተሠርይበት ታላቅ ምሥጢር ነው ። የሚታይ አፈጻጸም የማይታይ ጸጋ አለው። ያለ ጥምቀት የሥላሴን ልጅነት ለማግኘት አይቻልም።

ጥምቀት ማለት ሁለተኛ ልደት ማለት ነው ። ሰው አንድ ጊዜ በሥጋና በደም ከእናት ከአባቱ ይወለዳል። ይህም ሥጋና ደም መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ስለ ማይችል ሁለተኛ በውኃና በመንፈስ ከሥላሴ ይወለዳል። «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» ብሏል ። አንድ ሊቅ «ሰው ሦስት ጠባያት አሉት ። እነሱም ሥጋዊ ፤ ነፍሳዊ ፤ መንፈሳዊ ናቸው። የሥጋን ፍላጎት ሲከተል ሥጋዊ ፤ የዚህን ዓለም ፍላጎት ሲከተል ነፍሳዊ ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ ሲራመድ ግን መንፈሳዊ ይባላል ። ስለዚህ ሰው መኖር የሚገባው በመንፈሳዊ ዓላማ መሆን አለበት ። ለመካከለኛው ቦታ የለውም በሥጋዊ ዓላማ እንኳ ቢመራ በነፍሱ ጉዳት ከሚያገኘው በቀር የሥጋውን ፍላጎት ሊያረካ ይችላል» ብሏል ። ሰው በሥጋ የወለዱትን የአባትና የእናቱን ርስት ጉልት ለመውረስ ሕግ ይፈቅድለታል ። በጥምቀትም ሁለተኛ ከእግዚአብሔር በተወለደ ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ፤የመንግሥቱ ወራሽ ይሆናል።

ቅዱስ ጳውሎስ «ልጆች በሆናችሁ ጊዜ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ ፤ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም ፤ ልጅ ከሆንህም በክርስቶስ የመንግሥቱ ወራሽ ነህ ፤ አብርሃም ሁለት ልጆች ነበሩት አንዱ የባሪያዪቱ ልጅ ፤ ሁለተ



ኛው በተስፋ የተወለደው የእመቤቲቱ ልጅ ነበሩ ። ይህም ምሳሌ ነበር ሁለቱ ሴቶች ሁለቱ ኪዳኖች ናቸው። አንዲቱ ከደብረ ሲና የሆነችው ልጆችን ለባርነት የምትወልደው አጋር ናት ። ይህችም አጋር በዓረብ አገር ያለችው ደብረ ሲና ናት ። አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች ። ከልጆችዋ ጋር በባርነት ናትና፥ የላይኛዪቱ ኢየሩሳሌም ግን በነፃነት የምትኖር እናታችን ናት . . . . እንደ ይስሐቅ የተስፋ ቃል ልጆች ነን ፤ . . . , የገረዲቱ ልጆች ከእመቤቲቱ ልጆች ጋር አይወርሱምና . . . . ስለዚህ የእመቤቷ ልጆች ነን እንጂ የገረዲ ልጆች አይደለንም» ይላል ። ገላ ፬፡ ፯፡ ፳፱፡-፴ ።

ይህም ማለት በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለደ የእመቤቷ የወንጌል ልጅ ካልሆነ መንግሥቱን ለመውረስ አይችልም ማለት ነው ። ጥምቀት ዘርን ፤ ፆታን ፤ ቀለምን አይመለከትም ሁሉንም በትክክል ወደ ጌታው ያቀርባል ። ስለዚህ አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ «እናንት የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለበሳችሁ በዚያም አይሁዳዊም አረማዊም ባሪያም ጌታም ወንድ ሴትም የለም ሁላችሁም የአብርሃም ልጆች የተስፋው ወራሾች ናችሁ ። አይሁድም ፤ አረማዊም ባሪያዎችም ጌታዎችም ሁላችንም አንድ አካል ሁነን ተጠምቀናል ፤ ሁላችንም ከአንድ መንፈስ ጠጥተናል» ይላል ። ፩ኛ፡ ቆሮ፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ። ገላ፡ ፫፡ ፳፯—፳፱ ።

«እግዚአብሔር ሰውን በጥምቀቱ ያነጻዋል ፤ ይቀድሰዋል ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይወዳታል በጥምቀት

www.ethiopianorthodox.org

ነበሩ ። ለምሳሌ እነ ጳሊቃርጳስ የሰሚርናው፤ እነ ጠርጥሊያኖስ ፥ እነ ጳጳያስ የሂራጳሊሱ እነ ኤሬኔዮስ ነበሩ ። እነርሱም ለአረማውያን ፤ ለጠቢባን ለተማሩ ሰዎች የክርስትናን ትምህርት ለማስረዳት እንዲቻል ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያስፈልጋል ብለዋል ። እንደ እኔም አስተያየት ብርሃን እያለ ጨለማን የሚመርጥ ያለ አይመስለኝም ።

እርግጥ ነው ዕውቀት ሦስት ዓይነት ነው ። አንዱ የግኖስቲኮች የዕውቀት ፍልስፍና ሲሆን ፥ ሁለተኛው ዕውቀት ደግሞ የ ኤሬኔዎስ በሃይማኖት በኩል አምላካችንን የምናውቅበት ትምህርት ነው ። ሦስተኛ በሳይንስና በቴክኒዎሎጂ ሳይንቲስቶች የሚራቀቁበት ፤ ሊቃውንት በፍልስፍና የሚመረምሩበት ፥ መሪዎች በአስተዳደር የሚመሩበት ዕውቀት ነው ። ከግኖስቲኮች ዕውቀት በስተቀር ሁሉም አስፈላጊ ነው ። ሆኖም ዘለዓለማዊ ሕይወትን የምንወርስበት መንፈሳዊ ዕውቀት ይበልጣል ። ስለዚህ ኤሬኔዎስ ግኖስቲኮችን በመቃወም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በአንድ ትምህርት ነው ። የእግዚአብሔር ፍጥረት ፀሐይ በአንድ ጊዜ በዓለም ላይ እንደሚያበራ ፥ የክርስትና ትምህርትም በአንድ ጊዜ በዓለም ላይ ያበራል እውነትን ወደማወቅ ያደርሳል ። በዚህም መንፈስ የሚመራ መምህር የሚናገረውን አያጣም ። እግዚአብሔርንም የሚወድ ፤ ዕውነትን የሚፈልግ ወደ ዕውቀት ይደርሳል ፤ ዕለት ዕለትም ዕውቀት ያድግለታል ብለዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ እግዚአብሔር ልጅ ሃይማኖት አንድነትና እውቀት እስክንደርስ ድረስ . . . . ሕፃ



ናት እንዳንሆን ሞገድ ወዲያና ወዲህ እንደሚያገፋን ይላል ። ኤፌ. ፬ ፲፫—፲፬

በእስክንድርያ የዕውቀት ትምህርት ቤት የሚባል መንፈሳዊ ኮሌጅ ተከፍቶ ነበር ። የዚህ ትምህርት ቤት ዓላማ ወጣቶችን ለጠቢባን ፤ ለአረማውያን የክርስትናን ትምህርት ለማስረዳት እንዲችሉ ጠለቅ ባለ ዕውቀት ማሠልጠን ነበር ። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ቀሌምንጦስ ሃይማኖት ለአዋቂ ነው ብሏል ። ደቀ መዝሙሩ አርጌኒስም ዕውቀት ከሃይማኖት ይበልጣል ፡ ምክንያቱም አውቀው የሚያምኑት ስለሆነ ነው ይላል ። ስለዚህ በክርስትና ትምህርት የክርስቶስን ሰው መሆን ራሱንም ስለእሱ እንደሠዋለት ማወቅ ስላለበት ዕውቀት አስፈላጊ ነው ።

፪ኛ እምነት ። እምነት ማለት አንድ ነገር ቢታይም ባይታይም ይሆናል ብሎ ማመን ነው ። እግዚአብሔርን ማመን ግን ቀላል አይደለም ። አባ ሕርያቆስ «እግዚአብሔር ይህን ይመስላል ይህን ያህላል ልንለው አንችልም» እንዳለው ስለ እግዚአብሔር እንደ ቍጥር በመደመር ፤ በመቀነስ ፤ በማባዛት ፥ በማካፈል ወይም በጂኦሜትሪ፡ በመመዘን ፤ በመመጠን ፤ በመለኪት ፥ እንደ ሳይንስ አንዱን ኤለመንት ካንዱ ኤለመንት በመቀመምና በመቀላቀል በኬሚካል ሪአክሽን መልሱን ለማግኘት አንችልም ። ግን በሃይማኖት ኃያልነቱን ፤ ጠቢብነቱን አይተን ልናምነው እንችላለን ። ቅዱስ ጳውሎስ «ይህ ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠረ እናምናለን» ይላል ። ዕብ ፲፩ ፫

www.ethiopianorthodox.org

እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት ነው ። ፩ኛው ተሻጋሪ (an active) ፪ኛው የማይሻገር (a passaive) ነው፤ አንዱ እግዚአብሔርን ማመንና በሱም ዋጋን ማግኘት ሲሆን፤ ሁለተኛው ራስ በመታመን በራስ መታመንም ዋጋ ማግኘት ማለት ነው ። ሮሜ ፫, ፴፫። በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት የተስፋ እምነት ይባላል ። ይህም ጠቅላላው ዓላማ ወደፊት ለምናገኘው ተስፋ ራስን ወደ መግዛትና ታዛዥነት አቅርቦ መስጠት ነው ።

እግዚአብሔር ለኛ ሲል ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሕይወቱን እንደሠዋለት ማመን ፤ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች የመንግሥቱ ወራሾች እንሆናለን ። ለዚህም መግቢያው በሩ ጥምቀት መሆኑን ተናግሬአለሁ ።

፫ኛ ንስሐ ፤ አሁንም ወደ ጥምቀት ለመድረስ አንዱ ጐዳና ንስሐ ይቀርናል ። ንስሐ ማለት በሠራት ኃጢአት ተመልሶ መጸጸት ፤ ከአምላክ ዘንድ ይቅርታን መጠየቅ ማለት ነው ። ዮሐንስ ከምድረ በዳ እያስተማረ ሲመጣ ፤ «ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና» እያለ ያውጅ ነበር ። ጌታም ከምድረ በዳ ወደ ገሊላ ተመልሶ ማስተማር በጀመረበት ጊዜ «ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና» ሲል በዮሐንስ አዋጅ ትምህርቱን ጀመረ ። ቅዱስ ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ በአደረገው ስብከት «ንስሐ ግቡና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እያንዳንዳችሁ ተጠመቁ ጸጋውን ትወርሳላችሁና» በማለት የመጀመሪያውን ስብከት በንስሐ ጀመረ የሐ. ሥራ ፪, ፴፮ ።



ይህ ለትላልቆቹ በኃጢአት ለኖሩ ሰዎች ነበር ፤ ለሕፃናት ግን አንደኛ የሠሩት ኃጢአት በለመኖሩ ፤ ሁለተኛ ሕፃናት ስለሆኑ ይህ ቃል አይመለከታቸውም ።ሆኖም ወላጆች ሕፃናትን ሲያጠምቁ ቤተ ክርስቲያን ዋስ ታስጠራቸዋለች ። እነዚህም ዋሶች «የክርስትና አባትና የክርስትና እናት» ይባላሉ ። እነርሱም ለሕፃናቱ ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው ። ሕፃናት በሃይማኖት ፤ በሞራል ተጠብቀው እንዲያድጉ ማስተማር ዋና ተግባራቸው ነው ። ትልልቆቹ ከላይ እንዳልኩት ይማራሉ ፤ ያውቃሉ ፤ ያምናሉም በሠሩትም ኃጢአት እየተጸጸቱ በንስሓ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሔዱ የሚገባውን ጸሎት ያጠናሉ ፤ ሥርዓቱንም ይመለከታሉ ፤ የሚያጠኑትም ትምህርት ጸሎተ ሃይማኖትን ነው ። በመጀመሪያ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እናምናለን ፤ ሰይጣንን እንክደዋለን እያሉ ይጸልያሉ ። እስከሚጠመቁ ድረስ ፍሬ ቅዳሴ ሲደርስ ይወጣሉ በሥርዓተ ቅዳሴያችን ፃዑ ንዑሰ ክርስቲያን የሚባሉት እነዚህ ናቸው ። ጸሎቱን ካጠኑ ፤ ሥርዓቱን ከተመለከቱ በኋላ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እናምናለን ፤ በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን በማለት እምነታቸውን ገልጠው ይጠመቃሉ ። ለሕፃናት ግን መናገር ስለማይችሉ የክርስትና አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ጸሎተ ሃይማኖትን ይደግሙላቸዋል ። ከዚህ በኋላ ይጠመቃሉ ። በዚህ ዓይነት ለጥምቀት ዕውቀት ፤ እምነትና ንስሓ በጣም አስፈላጊዎች ሆነው ተገኝተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ነት አዲስ ስለ ነበር አብዛኛውን ጊዜ መጠመቅ የሚገባ
ቸው ትልልቆች ስለ ነበሩ ነው ። ሕፃናት ግን ወላጆቻ
ቸው ሲጠመቁ አብረው ይጠመቁ ነበር ፤ ይበልጠውንም
እምነት ከወላጆች ይጠበቅ ነበር ። ይህም ሲሆን ከላይ
እንደ ተባለው ጥምቀት የማያስፈልግ ቢሆን ኖሮ ቅዱስ
ጴጥሮስ ንስሐ ግቡና ተጠመቁ ካለው ቀጥሮ ወረድ ብሎ
ተስፋው ለእናንተና ለልጆቻችሁ በሩቅም ላሉት እግዚ
አብሔር አምላካችን ለጠራቸው ሁሉ ነው እንዴት ይል
ነበር ?

ሲጠመቁም የእግዚአብሔር ጥሪ ለሁሉም ስለሆነ
ከነልጆቻቸው ነበር ፤ ኤሬኔዎስም ጌታ ሕፃናትን ወደ
እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው ያለውን ጥምቀት
ነው ብሎ ተርጉሞታል ። ጠርጥልያኖስ ግን «ሕፃናት
ሳያምኑ ቢጠመቁ ሊጠቅማቸው አይችልም» ያለውን
ቤተ ክርስቲያን አልተቀበለችውም ። "ሕፃናት አምነው
እስኪጠመቁ ድረስ ጊዜ ስለሚወስድባቸው ደግሞ ከሥ
ላሴ ልጅነት ተለይተው ለመኖር ስለማያስፈልጋቸው
ሕፃናት መጠመቅ አለባቸው» ስትል ታስተምራለች
(የካርታጎ ካርቴጅ) ጳጳስ ቆጵርያኖስ ፪፻፶፫) ከአንድ ፊዱስ
ከተባለው ኤጲስ ቆጶስ «ከአስፈለገ "ሕፃናት ከ፰ ቀን
በፊት መጠመቅ ያስፈልጋቸዋል ወይ ? የሚል ጥያቄ
ቀርቦለት ነበር ። ቆጵርያኖስም ራሱ ሊቀ መንበር ሆኖ
ከ፷፮ ጳጳሳት ጋር በካርታጎ በአደረገው ሲኖዶስ ።ሕፃናት
ከተወለዱ በኋላ በሁለትና በሦስት ቀን መጠመቅ አያስ
ፈልጋቸውም ግን የአሪት የግዝረት ሥርዓት ይጠበቅ



ዘንድ በ፰ ቀን መጠመቅ አለባቸው ጥምቀትም እንደ
ሥርዓት የሚቈጠር ሳይሆን ልጆችን ከልጅነታቸው ጀምሮ
በአዕምሮአቸው ውስጥ ከሚገኘው ጉድለት ይጠብቃቸ
ዋል እርሱም ቶሎ ያድናቸዋል,, ሲል ለጥያቄው መልስ
ሰጥቷል ። እንደ ቆጵርያኖስ አስተያየት በአሪት ግዝረት
የአይሁድነት ምልክት ሲሆን የሚፈጸመውም በ፰ ቀን
ነበር ጥምቀትም የክርስቲያንነት ምልክት ስለሆነ ፤ በ፰
ቀን መጠመቅ ያስፈልጋል ማለቱ ነው ።

የቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ
፫፻፹ የሕፃናትን ጥምቀት ይደግፋል ጥምቀትንም አምላ
ካዊ ሕይወት ነው ብሎ ተርጕሞታል ። ባስልዮስ ዘቂሣ
ርያም ፫፻፸፱ የጎርጎርዮስን ሐሳብ ይደግፋል ። እሱም
"እሥራኤል የኤርትራን ባሕር ባይሻገሩ ኖሮ ከፈርዖን እጅ
ባላመለጡም ነበር። አንተም በጥምቀት ውኃ ካላለፍህ ከዲ
ያብሎስ ተገዥነት ልታመልጥ አትችልም,, ይላል ።

ይህ ሁሉንም ያመለክታል ዮሐንስ አፈወርቅም «ሕፃ
ናት ይጠመቁ ዘንድ ይገባል ። ጥምቀት ሕፃናትን ወደ
ቅድስና፤ ወደ ጽድቅ ፥ ወደእውነት፥ ወደ ክርስቶስ አንድነት
ያደርሳቸዋል የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች ያደር
ጋቸዋል» ብሏል ። አምብሮስ የሚባል የሚላን ጳጳስ
ክርስቶስ «ከውኃና ከመንፈስ ሁለተኛ ካልተወለደ የእግ
ዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ያለውን ሲተ
ረጕም «እግዚአብሔር የሚጠብቀው ሁሉንም ነው»
ብሏል ። አርጌንስ የሕፃናት ጥምቀትን ቢደግፍም የተለየ

www.ethiopianorthodox.org

አስተያየት አለው ። ይህም «ሕፃናት መጠመቅ የሚያስፈልጋቸው በኃጢአት ስለተወለዱ ነው» ይላል ። ከሱም ጋር ዳዊት «በኃጢአት ተፀንሼ በበደል ተወለድሁ» ያለውን መነሻ በማድረግ ሕፃናት በኃጢአት እንደሚወለዱ ጥቂቶች ያምኑበታል ግን ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት በተለየ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ይህ በኦሪት የነበረው የዘር ኃጢአት በክርስቶስ ሞት ጠፍቶአል በማለት በሐዲስ ኪዳን የራስ ኃጢአት እንጂ የዘር ኃጢአት አለመኖሩን ያምናሉ ። ግን የሕፃናት ጥምቀት የሚያስፈልገው ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው በቅድስና በዕውነት ፤ በመንፈስና በሞራል በሃይማኖት የአምላካችን ልጆች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ ነው ። ስለ ትምህርታቸውም የክርስትና አባትና እናት ይደረግላቸዋል። በዚህ ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት ከአንዳንዶቹ በስተቀር የሕፃናትን ጥምቀት ይቀበሉታል ።

## ምዕራፍ ፱

## የእኛ ቤተ ክርስቲያን

የእኛ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናትን ጥምቀት ከልብ ከመቀበሏም በላይ ስለ ሕፃናት ጥምቀት የተወሰነ ጊዜ አላት ። ወንድ ልጅ በ፵ ቀን ፤ ሴት ልጅ በ፹ ቀን ታጠምቃለች ። ለዚህም በቂ ምክንያት አላት ።

፩ኛ| አባቶቻችን እንደሚነግሩን አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ፤ ሔዋን በተፈጠረች በ፹ ቀኑዋ በማየ ሕይወት



ታጥበው ከሥላሴ ልጅነትን አግኝተው ወደ ገነት ገብተዋል ይባላል ። በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ወንድ ልጅ በ፵ ቀን ፤ ሴት ልጅ በ፹ ቀን ተጠምቀው የሥላሴን ልጅነት አግኝተው የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች እንዲሆኑ ታደርጋለች ።

፪ኛ| በኦሪት ልማድ ወላጆች ወንድን ልጅ በ፵ ቀኑ ፤ ሴትን ልጅ በ፹ ቀኑዋ ለቤተ መቅደስ የሚገባውን ዕጅ መንሻ መሥዋዕት ዕጉለ ርግብ ፡ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ለካህኑ አቅርበው ያስባርኳቸው ነበር ።

ጌታም በተወለደ ጊዜ በ፵ ቀኑ በዚሁ ልማድ መሠረት ለቤተ መቅደስ የሚገባውን መሥዋዕት የዋሊያና የርግብ ልጆች ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ሄደው ለካህኑ ሰጥተውታል ። ስምዖን የሚባል አንድ ሽማግሌ በቤተ መቅደሱ ተገኝቶ ጌታን ታቅፎ ከሽምግልናው ታድሶ ጌታውን እያመሰገነ እንደ ዋሊያ ሲዘል ውሏል ። ሊቃውንትም እንደሚሉት ስምዖን የክርስትና አባት ምሳሌ ነው ይባላል ። በዚህ ዓይነት በቤተ ክርስቲያናችን ወንድ ልጅ በተወለደ በ፵ ቀኑ ፤ ሴት በ፹ ቀኑዋ ለቤተ ክርስቲያን ከሚገባው መሥዋት ጋራ ወስደው ያጠምቋቸዋል ። በጥንት ጊዜ ሕፃናት ከተጠመቁ በኋላ ማርና ወተት ያቀምሷቸው ነበር ፤ ይህም ማርና ወተት የሚፈስባት የሰማያዊት ከነዓን ወራሾች መሆናቸውን ያመለክቱ ነበር ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ሕፃናት እንኳን ከ፵ ቀን በኋላ

www.ethiopianorthodox.org

ሞት የሚያሰጋቸው ከሆነ ከ፵ ቀን በፊት እንዲጠመቁ ታዛለች ። (ፍ·ት· ነገ)

## ምዕራፍ ፲

## ሥርዓተ ጥምቀት ፤

የጥምቀት ሥርዓት የሚፈጸመው በቤተ ክርስቲያን አማካይነት በጸሎትና በዝማሬ ነው ። ማጥመቅም የሚገባው ንጹሕ በሆነ ፈሳሽ ውኃ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማድረግ ነው ። ይህም ጌታ ሦስት ሌትና ሦስት መዓልት በከርሠ መቃብር አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው ። ሁለተኛ የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው።ዲዲስቅልያም በፈሳሽ ውኃ እንዲጠመቅ ያዛል ። ጌታ በፈሳሽ ውኃ ተጠምቋል፤ዲያቆኑ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን መኰንን በፈሳሽ ውኃ አጥምቆታል በዚህ ዓይነት በጥንት ጊዜ ሰዎች የሚጠመቁት በፈሳሽ ውኃ ነበር ግን ቀስ በቀስ ብዙ ችግር እያጋጠመ ስለሄደ እንደ ሥርዓቱ ለመፈጸም አልተቻለም ። አንደኛ ውኃ እንደ ልብ አይገኝም ነበር ምክንያቱም በጥንት ጊዜ በጠላት በወንበዴ ይህንና ይህን በመሳሰለው ችግር ከተማ፥ መንደርና ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ በተራራ ላይ ስለ ነበር ብዙ ጊዜ በቂ ውኃ አይገኝም ነበር ። ሁለተኛ ለሕፃናትና ለበሽተኞች በራስ ላይ በማፍሰስ ሰውነትን በመርጨት ማጥመቅ ተጀመረ ።



## ምዕራፍ ፲፩

## አጥማቂው ፤

ጳጳስ ወይም ቄስ ነው ። ጌታችን መጀመሪያ የማጥመቁን ሥልጣን ለሐዋርያት ሰጥቷል ። ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው የማጥመቅንና የመባረክን ሥልጣን ሰጥተዋል ።

ቤተ ክርስቲያናችን የማጥመቅን ሥልጣን ለጳጳሳትና ለቀሳውስት ብቻ ትሰጣለች ። ብዙ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ይህ በሰላም ጊዜ ነው ፤ ግን ካልተጠመቁ ድኅነተ ነፍስ ለማግኘት ስለማይቻል በችግር ጊዜ ማንኛውም ክርስቲያን ሴት ሳትቀር ሊያጠምቅ ይችላል ይላሉ ። ይህ በእኛ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው አስተያየት የለም ። ወደፊት ጥናት የሚያስፈልገው ነው ። እንደ ትምህርታችን በጥምቀት መንፈስ ቅዱስን ማሰጠት ለቀሳውትና ለጳጳሳት የተለየ ሥልጣን ነው ።

ለምሳሌ ዲያቆኑ ፊልጶስ በሰማርያ ያጠመቃቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ሳይወርድላቸው ቈይቶ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሄደው እጃቸውን በጫኑባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወርዶላቸዋል ።

ጳውሎስ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት አጥምቆ እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወርዶላቸዋል ። በጥንት ጊዜ አንድ ካህን አጥምቆ እጁን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ያሰጥ ነበር፥ በኋላ ግን ዕጅ በመጫን ፈንታ ሜሮን መቀባት ተተካ ።

www.ethiopianorthodox.org

ታዊና ትምህርታዊ ሥርዓቶች ሁሉ አፈጻጸሟ ራሱ እንደ ፊልም ፤ እንደ ሥዕል ይህን የሚደረገውንና የሚፈጸመውን ሥነ ሥርዓት የራቀውን አቅርቦ ፥ የረቀቀውን አጉልቶ ያሳያል ። በዚህ መሠረት የጥምቀትን በዓል የምናከብረው ወንዝ ወርደን ፥ ዳስ ጥለን ፥ ድንኳን ተክለን በደመቀ ማኅሌታዊ ሥነ ሥርዓት ነው ። ለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን በቂ ትርጉምና ምክንያት አላት ።

፮ኛ የጌታችንን ጥምቀት ለማስታወስ ነው ፤ ጌታችን ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ እንደተጠመቀ ፥ እኛም ወደ ወንዝ ወርደን ቅዱስ ያሬድ ከብሉይና ከሐዲስ አወጣጥቶ የዘመረውን ዝማሬና መዝሙር እየዘመርን ስለጌታ ጥምቀት የሚናገሩትን ከ፬ቱ ወንጌሎች በሌላም ክፍል የጥምቀት ዓረፍተ ነገሮችን የሚጠቅሱትን ክፍሎች እያነበብን ፤ እየጸለይን በተመስጦ እናከብረዋለን ። የዮርዳኖስ ውኃ በጌታ ጥምቀት ተቀድሶአል ። ይህን ምሳሌ በማስታወስ ካህናቱ በውኃው ላይ ስብሐተ እግዚአብሔር አድርሰው ይባርኩታል ፤ ይቀድሱታል ።

የተጸለየበትን የተባረከውንና የተቀደሰውን ውኃ ምእመናኑን ይረጩበታል ፥ ይህን በመመልከት አንዳንድ ሰዎች «ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ይጠመቃሉ» ይላሉ። ይህ ትርጉሙ ባይገባቸው ነው እንጂ ሁለተኛ ለመጠመቅ አይደለም ። የጌታችንን ጥምቀት ለማስታወስ ፤ መታሰቢያነቱን ለማክበር ነው ።



፯ኛ የጥምቀት በዓል የበዓለ መጸለት ምሳሌ ነው ።

አይሁድ ፫ት ታላላቅ በዓላት ነበሩዋቸው ። እነርሱም ፩ኛ ፋሲካ ፤ ፪ኛ በዓለ ሠዊት ፤ ፫ኛ በዓለ መጸለት ናቸው። በበዓለ ፋሲካ ትንሣኤ ፤ በበዓለ ሠዊት ጰራቅሊጦስ ፤ በበዓለ መጸለት ጥምቀት ተተክተዋል ። አይሁድ እነዚህን በዓላት ውጭ ወጥተው ዳስ ጥለው ድንኳን ተክለው ያከብሩዋቸው ነበር ። የእኛም ባህል አብዛኛው የተመሠረተው በኦሪት ሥርዓት ላይ ስለሆነ በዚሁ ምሳሌ የጥምቀትን በዓል የምናከብረው ወንዝ ወርደን ፤ ዳስ ጥለን ፤ ድንኳን ተክ[illegible] በማኅሌትና በዝማሬ ነው ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org